# እንቆቅልሽ

እታለሜ እንቆቅልሽ
በጄ በይኝ፣ ምን አውቅልሽ
ልጠይቅሽ ካፌ ይውጣ
አጉል ነገር መላ ያጣ፤

ማን ይበሉት ይህን ጎሳ
በስተኋላ የተነሳ
የማይዘሩ፣ የማይበሉት
የማይወዱ፣ የማይጠሉት
አያነሱ፣ ወይ አይጥሉት
አያወርዱ፣ ወይ አይሰቅሉት?

ያበምድር ልጅ የጥዋት ልሁቅ
ያምና እገሌ የትናንት ሊቅ
ከልሳን ቤት ከአድባር መንደር
ከወግ እምባ ከእድር ሰፈር
ያሩር ትንፋሽ ካልመለጣት
የቆፈን ጥርስ ከማይግጣት
ያቅኝ ኮቴ ካልዳመጣት
ለሰው አብራክ ከመረጣት
የእድሜ ጫና ካጎበጣት
ከኩሽ ገንዳ ዘሩ በቅሎ
በምድረ-አበሽ ጥርሱን ነቅሎ
በእናት አለም ስፍስፍ አንጀት
በአባት ድካም ሙሉ ማጀት
በእቴሜቴ የሎሚ ሽታ
በወንድም ጋሼ መከታ
በ«እንትፍ እደግ» በ«ካይን ያውጣህ»
«ለአይኔን ባይኔ ተድላ ያብቃህ
ጡሮ መጦር ይሁን እጣህ»
አድጎ፣ ደርጅቶ፣ ጎልምሶ
ለእሰየው አቅመ አዳም ደርሶ።

ምን ለክፎት ነው ወደማታ
ጋራ ዞሮ የነጎደው
ከባይተዋር ወግ ጨዋታ
ካላፈራው የለመደው
በስደት መዘዝ በሽታ
ስብእናውን የመረዘው
የባለአገር ማንነቱን
በመጤነት የሰረዘው
ያን ርቱዕ አንደበቱን
በባዕድ ልሳን የገነዘው?

ከፋ ደጉን ባወቀበት
ያባቱን ወግ ካስጨበጠው
ሰማይ ምድሩን በለየበት
የእናት ቋንቋ ካጠመቀው
ከጽንፍ አለም ቁራሽ መሬት
ስሩን ተክሎ ካስቀመጠው
ጣም እንከኑን ከሚያውቁለት
ወገን እቅፍ ከሸጎጠው
ከእጣ ፈቃድ ተቃቅሮ
ለርሱነቱ ከመረጠው።

ምን ገዶት ነው መዋተቱ
መኩሪያ ቅርሱን ገደል ከትቶ
ያመለጠው የብብቱ
የቆጥ ሲሳይ ተመልክቶ
በፋይዳቢስ ጉርብትና
በናፍቆት ጣር ተብከንክኖ
የእምዬን አይን በስተርጅና
በእይታ ራብ አመክኖ።
ማን መክሮት ነው አይዞህ ብሎት
ያለቀየው የከተመው
ተድላ ከሆድ ያብብ መስሎት
ከማያውቁት የገጠመው
ያብሮ አደጉን ጓደኝነት
እንደዘበት የረገጠው
በውርጭ አለም ቤተኝነት
የምድሩን ጣይ የለወጠው
ለከርስ አምላክ ግብር ታምኖ
ህሊናውን ያዘቀጠው
ነፍስያውን አመንምኖ
ትከሻውን ያሳበጠው?

ፋሲል ይትባረክ